እ.ኢትዮ.አ. የካቲት 12 ቀን 2002ዓ.ም.
ጃንዋሪ 19/2010

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

ለሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት ፤
ካሊፎርኒያ

በሲያትል ለመንበረ-ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል መንበረ-ጵጵስና ጽሕፈት ቤት፤
ሲያትል

የብጹዕ አባታችንን የአቡነ ዜና ማርቆስን ዕረፍት በተመለከተ የተሰማንን እጅግ ጥልቅና መሪር የሆነ ሐዘናችንን ስንገልጽ፤ ለቤተ-ክርስቲያንና ለእኛም የቤተ-ክርስቲያን ልጆች ቸሩ አምላካችን እግዚአብሄር ብርታቱንና ጽናቱን እንዲሰጠን በጸሎት በመጠየቅ ነው።

ክብር ይግባውና ጌታችን፣ አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ቁጥር 16 «...መልካሙን *ሥራ*ችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ። ...» በማለት እንደ ተናገረው፤ የብጹዕ አባታችንም መልካም *ሥራ*ቸው ከቅድስት ሃገር ከኢትዮጵያ ጀምሮ እስከ ውጭ ሃገር ድረስ በሰፊው እየታየና እያንፀባረቀ ለትውልድ እየተላለፈ ይገኛል።

እንግዲህ ብጹዕ አባታችን ለጊዜው ከኛ በአጸደ-ነፍስ ቢለዩም በእግዚአብሄር ፊት ሕያው ናቸው፤ የድካማቸውንም ዋጋ መኮንነ-ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት የብርሃን አክሊል አቀዳጅቶ ይከፍላቸዋል ።

ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 9«...የምንሞት ስንመስል እነሆ ሕያዋን ነን።...» በማለት በሰፊው የገለፀው፤ ለጊዜው በሞት በአጸደ-*ሥጋ* ብንለይ በእግዚአብሄር ፊትና በሰማያዊው ቤታችን ሕያዋን መሆናችንን ነው።

ጌታችንም፦ «...ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ። የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳን ሕያው ይሆናል።ሕያው የሆነ ሁሉ ለዘላለም አይሞትም ...» ዮሐ.11፥25-26 ሲል ስለ ትንሳኤና ሕይወት አስተምሮናል ።

ስለዚህ ማጽናናት ባሕርዩ የሆነው አምላካችን ለብጹዓን አባቶቻችን ለሊቃነ-ጳጳሳት፣ ለአበው ካህናት፣ ለዲያቆናት፣ ለመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ምዕመናንና ምዕመናት መጽናናቱን እንዲሰጥልኝ፤ የአባታችንን ነፍስ ዕረፍተ-ነፍስ ሰጥቶ ከቅዱሳን ሐዋርያት ጋር እንዲያሳርፍልን፤ ለኛም ለጠቅላላው ሕዝበ-ክርስቲያን የብጹዕነታቸውን ጸሎት፣ በረከትና ሀብተ-ረድኤት እንዲያድለን የእግዚአብሄር መልካም ፈቃዱ ይሁንልን አሜን ።

ከሊቀ-ካህናት አስተርአየ ካሣ እንዲሁም በጀርመን ሃገር በቪስባደንና አካባቢው ከሚኖሩ ምዕመናንና ምዕመናት ።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com